## <u>የሰሞኑ ትዝብት</u>

ሀማ ቱማ

ትምጣልኝ ቢዮንሴ የልቤ ንግሥት
ይውጣላት ታቦቱ በቀትር ይቀደስ
ከጎኔ ቁጭ ብላ ትበለኝ ወንደርፉል
ካህን ያርግድላት ያች የእኔ ቅምጥል ።
ጥላሁን ሞተ አሉ ታዲያ ምን ይጠበስ
ጳውሎስ እንደሁ አይሄድ ከሥላሴ ድረስ
በትግሪኛ አይዘፍን ወይ በእንግሊዝኛ
ጌት ዳውን አልችልበት እኔ በአማርኛ።

## <u>ኩዴታ-- ግድያ</u>

ታስቦ ነበረ መፈንቅለ መንግሥት
በ አስራ አምስት ክላሺን ቦምቡም ነበር ስድስት
በሲቪሎች መንጋ በአኩራፊ ወታደሮች
ለተጠላ መንግሥት መች አንሰው አርባዎች?
ማመን ካቃታችሁ በኩዴታ ወሬ
ሳታመካኝ ብላኝ የአያ ጅቦ ወሬ
ዜናው ይለወጣል ሙከራው ግድያ
ሚኒስቴር ለመድፋት ሲነጋ ሲጠባ
አወይ ባደረገው ለምትሉ ሁሉ
ሰዎቹን ይዘናል እርማችሁን አውጡ።

## <u>የአሳማ ኢንፍሉዌንዛ</u>

ቫክሲኑ ክኒኑ በየመጋዘኑ
ተጠቃሚ ጠፍቶ ሲያፈጥ መባከኑ
የወረርሽኝ ወሬ ሽብር ዓለም አቀፍ
ውጉኝ ባይ ሲበዛ ድንጉጥ ሲንሰፈሰፍ
ገበያው ሲደራ ገንዘብ ሲትረፈረፍ
የአሳማ ፍሉ መጣባችሁ ቡታ
ምኑ ሊያስገርመን የጠበቅነው ዜና?
ጥቁር ሰው በዋይት ሀውስ ባለቤት ሲሆን
አሳማ ይበራል ተብሎ አልነበር?